# የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 እና 6

1. ጌታችን መፃጉዕን የፈወሰበት መጠመቂያ ወይም ቦታ ምን ይባላል?
ሀ) ቅልብንትራ ለ) ቤተ ሳይዳ ሐ) ቤተ ሣህል መ) ሁሉም መልስ ናቸው

2. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መፃጉዕ ሊድን እንድሚፈልግ እያወቀ “ልትድን ትወዳለህን?” ብሎ የጠየቀው ለምንድን ነው?
ሀ) አላዋቂ የነበረን ሥጋ እንደተዋሐደ ለማጠየቅ
ለ) በዕለተ ዓርብ የሚመታው ነውና ያዳነህን ለምን መታኸው ቢሉት እራሱ አዳነኝ እንጂ እኔ አድነኝ ብዬው አይደለም የፈወሰኝ እንዳይል
ሐ) ነጻ ፈቃድን የማይጋፋ መሆኑን ሊያሳይ
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

3. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ መልአኩ ወደ መጠመቂያው የሚወርደው ለምንድን ነበር?
ሀ) ውኃውን ለመቀደስ ለ) መስዋዕትን ለማሳረግ ሐ) ሲጎድል ለመሙላት መ) ሀ እና ለ

4. ስለ ቤተ ሳይዳ መጠመቂያ ምሳሌነት ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) መልአኩ የቀሳውስት፣ ውኃ የጥምቀት
ለ) 5 እርከን የ5ቱ አዕማደ ምስጢር
ሐ) 5 ድውያን የ5ቱ ዖታ ምዕመናን(አዕሩግ፣ ወራዙት፣ አንስት፣ ካህናት፣ መነኮሳት)
መ) መልሱ አልተሰጠም

5. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ የአልጋ ቁራኛ የነበረው ሰው ለስንት አመታት ነበር የታመመው?
ሀ) 25 ለ) 38 ሐ) 40 መ) 15

6. ጌታ መጻጉዕን ያዳነበት ዕለት መቼ ነበር?
ሀ) ሰኞ ለ) እሑድ ሐ) ቅዳሜ መ) ሐሙስ

7. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ለእነዚህ ሰዎች የምናበላቸው እንጀራ ከወዴት እንግዛ?" ብሎ የጠየቀው ማንን ነው?
ሀ) ናትናኤል ለ) ፊልጶስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ዮሐንስ

8. ጌታችን ለሕዝቡ የሚሆን ምግብ ከወዴት እንግዛ ብሎ በጠየቀ ጊዜ አምስት የገብስ እንጀራ እና ሁለት ዓሣ መኖሩን የተናገረው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ፊልጶስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) እንድርያስ መ) ዮሐንስ

9. ጌታችን ምግቡን አበርክቶ ሕዝቡን ካበላ በኋላ ትቷቸው ወደ ተራራ የሄደው ለምንድነው?
ሀ) ሊያነግሱት እንደወደዱ አውቆባቸው
ለ) ሊገድሉት እንደሚፈልጉ ስላወቀባቸው
ሐ) እንደገና ምግብ እንዲያበረክትላቸው እንዳይጠይቁት
መ) ብቻውን ለመጸለይ ፈልጎ

10. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ጌታ ምስክሮች ያላቸው እነማንን/ ምንን ነው?
ሀ) አብን ለ) ተአምራቱን ሐ) መጻሕፍት መ) ሁሉም

11. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ ጌታ ከደዌው ያዳነውን ሰው በምኩራብ ሲያገኘው ምን ተናገረው?
ሀ) በመፈወሱ ምን ያህል እንደተደሰተ ጠየቀው
ለ) የነፍስ ደዌ እንዳያገኘው ደግሞ እንዳይበድል አስጠነቀቀው
ሐ) ለምን ወደ ምኩራብ እንደገባ እየተቆጣ ጠየቀው
መ) ሃብቱ እንዲበዛለት ባረከው

12. አይሁድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመግደል ከሚሹበት ምክንያቶች ውስጥ የሆነው የቱ ነው?
ሀ)ሰንበትን ይሽራል ብለው ስላሰቡ
ለ)እግዚአብሔርን አባቴ ይላል ብለው
ሐ)ተአምር ስላደረገ
መ)ሀ እና ለ

13. ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረው ማን ነው?
ሀ)መጥመቁ ዮሐንስ
ለ)እራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
ሐ)የአስቆሮቱ ይሁዳ
መ)ሁሉም

14. "እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደስ ሊላችሁ ወደዳችሁ"ይሄን ምስክርነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሰከረው ስለማን ነው?
ሀ)ስለእራሱ
ለ)ስለመጥመቁ ዮሐንስ
ሐ)ስለፊሊጶስ
መ)ስለአውግስጢኖስ

15. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን ስላልተቀበሉት በአብ ዘንድ የሚከሳቸው ማን ነው ብሎ ተናገረ?
ሀ)ኤልያስ ለ)ዘካርያስ ሐ)ኢያሱ መ)ሙሴ

16. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሊያነግሡት የፈለጉት መቼ ነው?
ሀ)ድውያንን ሲፈውስ ለ)እንጀራ አበርክቶ ሲመግብ ሐ)ሙት ሲያስነሳ መ)ሁሉም

17. ብዙዎችን ወደሓላ ያሸሻቸው የጌታችን ቃል የቱ ነው?
ሀ)ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ
ለ)ሙሴ የጻፈውን ካላመናቹ የእኔን ቃል እንዴት ታምናላችሁ
ሐ)አባቶቻችሁ መናን ከሰማይ ተመገቡ
መ)መልስ አልተሰጠም

18. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ "እኔ ነኝ" ብሎ ከተናገራቸው ውስጥ የሆነው የቱ ነው?
ሀ)የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ለ)እኔ የወይን ግንድ ነኝ ሐ)እኔ የዓለም ብርሀን ነኝ መ)ሁሉም

19. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ላይ ከፈፀማቸው ተአምራት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ)በባሕር ላይ መሄዱ
ለ)እንጀራ አበርክቶ መመገቡ
ሐ)አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ብሎ ማዳኑ
መ)ሀ እና ለ

20. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6:35 ላይ ያለው "ሁሉም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተማሩ ይሆናሉ"የሚለው ቃል አስቀድሞ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተነግሯል?
ሀ)ኦሪት ዘፀአት 16:4 ለ)መዝሙር 77:24 ሐ)ትንቢተ ኢሳይያስ 54:13 መ)መልስ አልተሰጠም